# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ኤፌሶን ሰዎች

## ጥናት 4 (1፣3-14) ሠራተኞችና አማኞች

*ማሳሰቢያ:- በዚህ ክፍል ውስጥ ለማየት የምንሞክረው፣ በጥናታችን ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን ሰብዕት/persons እና መንፈሳዊ በረከቶቹ ወደ እኛ እንዲደርሱ እነርሱ ያበረከቱትን የሥራ ድርሻ ነው: : ይሄም ማለት ለማየት የምንሞክረው በዚህ በጥናታችን ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩትን ሥራዎቻቸውን እንጂ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ የተጠቀሱትን አይደለም: :*

በዚህ በጥናታችን ክፍል ውስጥ 4 አይነት ሰብዕት/persons እና ለመንፈሳዊ በረከቶቹም እውን መሆን፣ እነዚህ ሰብዕት/persons ያበረከቱት *ሥራ* ተገልጾአል:-

1.አብ
- ሀ)የአብ የሥራ ድርሻ
  1. *መንፈሳዊ በረከቶቹ ሁሉ ከእርሱ ነው የመጡት ወይም የመንፈሳዊ በረከቶቹ ሁሉ ምንጭና ባራኪ አብ ነው: :*
     - *"...በመንፈሳዊ በረከት **ሁሉ** የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ: :"* ኤፌ 1፣3
     - *"...በክርስቶስ መረጠን: :"* ኤፌ 1፣4
     - *"...ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን: :"* ኤፌ 1፣5
     - *"ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን: :"* ኤፌ 1፣8
     - *"...የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና..."* ኤፌ 1፣9

  2. በክርስቶስ ለተሠሩት *ሥራዎች* ሁሉ እቅድና ፕላን አውጪ አብ ነው: : የተጠቀሱትም *መንፈሳዊ በረከቶች* ሁሉ እውን የሆኑት እንደ እርሱ አሳብና *ፈቃድ* ነው: :
     - *"በክርስቶስ ለማድረግ እንደወደደ እንደ አሳቡ..."* ኤፌ 1፣9
     - *"...በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም..."* ኤፌ 1፣10
     - *"እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳብ..."* ኤፌ 1፣11

- ለ)አብ ከላይ የተጠቀሱትን *ሥራዎች* እንዲያከናውን ያነሳሳው ነገር (motive)
  1. ፍቅር ኤፌ 1፣4: : በድሮው የአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም "በፍቅር" የሚለው ቃል እኛ በፍቅር እንድንሆን የሚለውን ትርጉም የሚይዝ ቢያስመስልም፣ በኦርጂናሉ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ግን ይህ ቃል የአብን ፍቅር የሚያሳይ ነው: : ስለዚህም በአዲሱ መደበኛ ትርጉም በቁጥር 4-5 ላይ አብ በፍቅር እንደወሰነን ግልጽ ያደርገዋል: : "...በፍቅር፣ *በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ፣* እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን": : ስለዚህ እግዚአብሔር በመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ እንዲባርከን ያነሳሳው ዋና ነገር ፍቅር ነው: :

  2. ይህን ለማድረግ የአብ በጎ ፈቃድ ስለሆነ ወይም ይህንን ለማድረግ ስለወደደ
     - *"በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ..."* ኤፌ 1፣5
     - *"በክርስቶስም ለማድረግ እንደወደደ..."* ኤፌ 1፣9
     - *"እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳብ..."* ኤፌ 1፣11

- ሐ)አብ መንፈሳዊ በረከቶቹን የባረከበት ሁኔታ
  - ከእኛ በጎ ሥራ ወይም መልካምነት ሳይሆን ከጸጋው ብዛት ነው
    - *"ዓለም ሳይፈጠር..."* ኤፌ 1፣4
    - *"...አስቀድሞ ወሰነን: :"* ኤፌ 1፣5
    - *"...እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር..."* ኤፌ 1፣6
    - *"...እንደ ጸጋው ባለጠግነት መጠን..."* ኤፌ 1፣7
    - *"ጸጋውንም ... አበዛልን: :"* ኤፌ 1፣8

- መ)አብ መንፈሳዊ በረከቶቹን ሁሉ የባረከበት ምክንያት
  - *"...እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ: :"* ኤፌ 1፣6
    - በዚህ ክፍል ክብር የሚለው ጥሬ ቃል ትርጉሙ:- በሌሎች ዘንድ መመስገንን፣ መከበርን፣ መወደስን፣ መሞገስን፣ መደነቅን ወዘተ የሚያነሳሳ ማናቸውም መልካም ነገር ወይም የተለየ ነገር ወዘተ ነው: :

- ጸጋው የሚያድን ወይም የሚምር መሆኑ ራሱ አንዱ የጸጋው ክብር ነው:: ጸጋው ግን ከምህረትና ከይቅርታ ያለፈ የተትረፈረፈ፣ የልጅነት ስልጣን የሚሰጥ፣ ርስትን የሚያወርስ፣ ጥበብንና ማስተዋልን የሚሰጥ ወዘተ ነው:: እነዚም ነገሮች የጸጋው ክብር ናቸው::
- "...እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው::" ኤፌ 1፣12
  - እዚህ ላይ የተጠቀሰውን አባባል በተለያየ ሁኔታ ልንረዳው እንችላለን:: በተለይ ግን በእኛ በሠራው ሥራ እግዚአብሔር በእኛም፣ በመላእክትም በፍጥረትም ሁሉ ክብሩ እንዲመሰገን ነው:: ይሄም እኛ ራሳችን የምስጋና ምክንያት እንድንሆን:: ራእይ 5፣8-14
- "...ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል::" ኤፌ 1፣14
  - እግዚአብሔር በሠራው ሥራ ፍጥረት ሁሉ የእርሱን ጸጋ፣ መልካምነት፣ ምሕረት ወዘተ ወይም ክብር እንዲያመሰግኑ ነው::

ማጠቃለያ:- አብ የመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ ምንጭ እንዲሁም እቅድ አውጪ ነው:: ይህንን ሁሉ ያደረገውም ከፍቅሩና ከበጎ ፈቃዱ የተነሳ ነው:: በጎነቱ ስላነሳሳው፣ ጸጋው ብዙ ስለሆነ እንጂ ከእኛ ማንነትና መልካምነት አይደለም:: ስለዚህም እንዲያው ባደረገው ሥራ ሁሉ ክብሩንና ምስጋናውን ሊወስድ የሚገባው እርሱ ነው::

2.ክርስቶስ/ወልድ

- ሀ)መንፈሳዊ በረከቶች *ሁሉ* (በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ስድስቱም በረከቶች በሙሉ) የተባረክነው በክርስቶስ (በክርስቶስ ውስጥ፣ በክርስቶስ አማካኝነት፣ በክርስቶስ ሥራ፣ በክርስቶስ በኩል ወዘተ) ነው::
  - "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን..." ኤፌ 1፣3
  - "...በክርስቶስ መረጠን::" ኤፌ 1፣4
  - "...በኢየሱስ ክርስቶስ...ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን::" ኤፌ 1፣5
  - "በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን ጸጋ..." ኤፌ 1፣6
  - "በውድ ልጁም...በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት::" ኤፌ 1፣7
  - "...በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን::" ኤፌ 1፣11
  - "...በክርስቶስ አምናችሁ፣ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ..." ኤፌ 1፣13

- ለ)ክርስቶስ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድና ፕላን መፈጸሚያ ነው::
  - "በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም፣ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው::" ኤፌ 1፣10

ማጠቃለያ:- ይህ በክርስቶስ ወይም በልጁ ወዘተ የሚለው ቃል ከ10 ጊዜ በላይ በዚህ ክፍል ውስጥ ተጠቅሷል:: በዚህም፣ ምንም አይነት የእግዚአብሔር በረከት ከክርስቶስ ውጪ እንደሌለ ጸሐፊው ለማሳየት እንደፈለገ እንገነዘባለን:: እውነተኛው የወይን ግንድ ክርስቶስ ነውና (ዮሐ 15፣1-11):: በረከቱ ወደ ሰዎች እንዲመጣ ዋናው ቅድመ ሁኔታ የክርስቶስ የመስቀሉ ሥራ ነው:: እግዚአብሔር የአለምን ሩጫና የዘላለም ሃሳቡን የሚቋጨው በክርስቶስ ነው:: ይሄውም ሁሉም ከክርስቶስ ራስነት ስር ሲገዙ:: በዚህ ሁሉ ልንረዳ የሚገባን፣ አብ ለሰው ልጆች መፍትሔንና በረከትን ለማምጣት ያቀደውንና ያሰበውን ሁሉ የፈጸመው በክርስቶስ ነው:: እግዚአብሔር ጥንትም ቢሆን፣ አለማትንና ፍጥረታትን ለመፍጠር ሲያቅድ ይህን እቅዱን የፈጸመው ወይም ተግባራዊ ያደረገው በክርስቶስ ነበር (ዮሐ 1፣1-2 ዕብ 1፣1-2 ቆላ 1፣13-17):: ስለዚህ ክርስቶስ ማናቸውንም እቅዱን የሚፈጽምበት የእግዚአብሔር ጥበብና ዘዴ ነው:: ለዚህም ነው የእስራኤል ልጆች በበረሃ ጉዞአቸው በገጠማቸው ማናቸውም ችግር እንደ መፍትሄነት እግዚአብሔር የሚያመለክታቸው የነበረው ክርስቶስን ነበር (ዮሐ 3፣14-15 1ቆሮ 10፣4 ዮሐ 6፣31-35)::

3.መንፈስ ቅዱስ

እግዚአብሔር ለእኛ ርስት እንዳዘጋጀልን የሚያረጋግጥ፣ የሚመሰክርና በረከቱን በሕይወታችን እውን እንዲሆን ወይም ለእኛ ሕይወት ትርጉም እንዲሰጥ ከሕይወታችን ጋር የሚያዛምድ ነው:: በዚህም ለእኛ ተስፋ የሚሰጠን ነው::

- "...በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፣ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው..." ኤፌ 1፣13-14
- "የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል::" ሮሜ 8፣16

ማጠቃለያ:- ያለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ አብ በክርስቶስ የሠራው ሥራ ከእኛ ጋር አይዛመድም 1ቆሮ 12፣3:: የእግዚአብሔር ሥራ ከሕይወታችን ጋር ተዋሕዶ ለእኛ ትርጉም እንዲኖረው የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው:: እርሱ ነው እግዚአብሔር የሠራልንንና ሊያደርግልን ያሰበውን ሥራ በሕይወታችን እውን በማድረግ እውነተኛ ተስፋ የሚሰጠን:: ያለ እርሱ እግዚአብሔር ያደረገልን ነገር ሁሉ ለእኛ ምንም ትርጉም አይሰጠንም::

4.አማኞች

እግዚአብሔር የባረከን በረከት ወደ አማኞች እንዲመጣ የአማኞች ድርሻ፣ በክርስቶስ ማመን ወይም በእርሱ ተስፋ ማድረግ በቻ ነው::

- "...በክርስቶስ...ተስፋ ያደረግን እኛ..." ኤፌ 1፣12
- "እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፣ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፣ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ..." ኤፌ 1፣13

እዚህ ላይ ልብ ልንል የሚገባው የአማኞች ዋና ድርሻ በክርስቶስ ማመን ነው:: እምነት ደግሞ ሥራ አይደለም ሮሜ 4፣1-5:: ይህ የጥናታችን ክፍል እንገዲህ በሥራና በእምነት ወይም በሠራተኞችና በአማኞች የተከፈለ ነው:: መንፈሳዊ በረከቶቹ ሁሉ ወደ እኛ እንዲደርሱ የሚያስፈልጉትን ሥራዎች ሁሉ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ተከፋፍለውት እንመለከታለን:: ለአማኞች የቀረላቸው ድርሻ ቢኖር ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ ላይ ያለ እምነት ነው:: ስለዚህ ጸሐፊው ደጋግሞ አብ ከበጎ ፈቃዱ፣ ከፍቅሩና ከማንነቱ የተነሳ ለክብሩ በክርስቶስ እንደባረከን በሰፊው ሲገልጽ የአማኞችን ድርሻ ግን በእምነት ላይ ብቻ ወስኖታል:: ይህም መንፈሳዊ በረከቶችን የተባረክነው ከእኛ ማንነትና ከመልካም ሥራችን ሳይሆን ከእግዚአብሔር ማንነትና ጸጋ የተነሳ መሆኑን ያስገነዝበናል:: አማኝ ሁሉ ከሁሉም በፊት በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ማረፍ አለበት:: እግዚአብሔር ያለ እኛ ሥራና ያለ እኛ ማንነት እንደተቀበለንና እንደወደደን አምነን በእርሱ መልካምነት ላይ ልንደገፍ ይገባናል:: እግዚአብሔር እንዲቀበለን ከክርስቶስ መስዋዕት ሌላ ተጨማሪ መሥዋዕት፣ እግዚአብሔር ራሱ ከምህረቱ ከሠራልን ሥራ ሌላ ተጨማሪ የእኛ ሥራ አያስፈልግም:: በጌታ ከምንሮጠው ከማናቸውም ሩጫ በፊት ይህ ለሕይወታችን መሠረት ሊሆን ይገባል:: ክርስትና ከማረፍ፣ ከመወደድ እንዲሁም ከበረከት ነው የሚጀምረው::